# ብረትን ያቀለጠ ወርቅን ያነጠረ ህዝባዊ ስብሰባ

*ከሥርጉት ሥላሴ*
*ሰኔ 2001 ዓ.ም.*

የወያኔውን አሰተዳደር ህሊናውን በቁንጣን ቁርጠት ያፈነ፤ ያተራመሰ፤ ያደናበረ ሕዘባዊ ስብሰባ በአውሮፓ እና በካናዳ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

በአውሮፓ፤ ... በሀገረ ሆላንድ፤ በሀገረ ጀርመን፤ በሀገረ ሲዊዲን፤ በሀገረ ስዊዘርላንድ በታላቋ ብሪታንያ በወርሃ ግንቦት ግንቦት 7 ወርቅን አነጠረበት፤ ብረትን አቀለጠበት። አሁን ደግሞ በሰኔ ወር መግቢያ፤ በሀገረ ካናዳ ምርቱን ያፈሳል! አዎን የነቃ ህሊና ለግዳጅ ዝግጁ የሚያደርግ አቻ የለሽ መርህ ነው!

ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይንም ግንባር ወይንም ንቅናቄ የድርጅታዊ ብቃቱ ልክነት ወቄቱ የሚለካው ህሊናዊ ሁነቶችን ከድርጅታዊ ሕይወት ጋር በውል በታቀደ በድርጊት ሲያከብር ብቻ ነው።

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባላቱም ሆኑ ደጋፊዎቹ ከሰነዶቹ ጋር በቅርበት ተገናኝተው ፈትሸው እና በልተው ወደ አጥቂ ሠራዊትነት መሸጋገር የሚችሉት ህሊናዊ መሰናዶችን በነጠረ ቅድመ ዝግጅት ሲተገበር ብቻ ነው!

**የህሊና ብቃት እድገትን ማመጣጠን ...**

... የድርጅትን የድል እርካብ ለማሰገኘት ፍጥነቱን ከመጨመሩም በላይ፤ አባላቱንም ሆኑ ደጋፊዎቹን ዓይናማ ያደርጋቸዋል። በመሆን ቤተኞቹ መንገዳቸውን አውቀው ትጥቅ እና ስንቃቸውን በማሟላት ጠላታቸውን ሙት መሬት ላይ ረብርበው ገዢን መሬት እራሳቸው ለመቆጣጠር የሚያስችል አንቱ የተባለለት የብቁ ፓርቲ መርህ ነው። ይህን የዘለለ ወይንም ግምቱን ያሳነሰ ፓርቲ ውሃ የበላው ቅል መሆኑ አይቀሬ ነው።

በመርህ ደረጃ ለፓርቲው እድገት እና ጥንካሬ ጉልበት በሚሰጡ ጉዳዮች ላይ የተገባውን አተኩሮት መስጠት መቻል የአመራሩን የብቃት ደረጃ ከማሰደጉም በላይ አባላቱን ሆነ ደጋፊ አባላትን እንዲሁም የአመራር አካላትን የህሊና ብቃት ማመጣጠን የሚያስችል ልዩ ፍፁም ልዩ የገቢር ቅመም ነው።

አንዳንድ ጊዜ የመሪዎች፤ አባላትን በሰፋ የህሊና ብቃት መብለጥ ወይንም ከሚመሩት አነሶ መገኘት በፓርቲው የተስፋ ጉዞ ላይ አቢይ ሳንክ የሚፈጥር ይሆናል ።

ስለሆነም በሁለቱም በኩል ያለውን የውስጥ ጥንካሬ እና ተመክሮ፤ እንዲሁም የፅናትን ልክ ማመጣጥን የሚቻልው እውነተኛ የሆነው ፓርቲ ለአባላቱ እና ለደገፊዎቹ እንዲሁም መሀል ላይ ለተጎለቱ ህሊናዎች ሁሉ ገባሪ አቃቤት ሲሆን ነው፤ ህዝባዊ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት ማደራጀት እና ለዒላማ ማሰናዳት ... ቀዳሚ ተልዕኮው ሊሆን ይገባል።

ስለሆነም ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ባልተራራቀ ጊዜ ለመርሁ የህሊናዊ ሁኔታዎች ሁነኛ መሆን ከአንድ የላቀ ፓርቲ ከነደፈው መርሀ ግብር የሚጠበቅ በኽረ ጉዳይ ነው።

**የሕዝባዊ ስብሰባዎች ፋይዳ እና ዕሴት ጥልቅ ነው ...... የሚያሰገኙት ... የሀሳብ ውህደት፤** የሚፈጠሩት የባለቤትን ስሜት የሚወልዱት የነጠረ ብሂራዊ ስሜት፤ የሚያመርቱት ቤተሰባዊ ፍቅር፣ የሚወልዱት የፅናት ልጅ መስፈርት ሊወጣለት አይችልም።

ስለዚህም ግንቦት 7 ንቅናቄ በተገኘባቸው ዓውዶች ሁሉ በእርገጠኝነት መናገር የሚቻለው ነገር መርሁ እና ንቅናቄው ተገናኝተው አትራፊ መሆን መቻሉን ነው። የእያንዳንዱ ስሜታዊ ህዋስ ቢመረመር ከቀደመው የህሊና ብቃት ከፍ ማለቱን ነው።

የውስጥ ውስጥነት ተሀድሶ መፍለቂ ነው። እኔ እራሴ ለናሙና የወሰድኳቸው ግለሰቦችን በሁሉም ቦታ ያለውን በምዕናቤ ስቃኝ ውጤቱ ዝቀሽ ነው።

በሌላ በኩል ድግሞ  ሕዝባዊው ስብሰባዎች ፤ … ደንባራ፣ ደንባሳ፣ ደብዛዛ፣ ጠንጋራ፣ ቀዝቃዛ ፍላጎትን አንጋለው ይቀልቡ ለነበሩ ወገኖች በጊዜ ሂሳባቸውን አወራርደው መቀላቀል ችለዋል። የቆሙበትን ተዛነፍ ገጠመኝን እንዲቃኙትም በሩን ከፍቶላቸዋል። እራሳቸውን የወቀሱም ቅን ኢትዮጵያውያንም ተገኝተውበታል።
በዕውነት ሕዝባዊ ስብሰባው አፍረቷል።

በገዢው ጎሰኛ ድርጅት በወያኔ ዘርፍ ለተሰለፉት አባላት አሳመዎችም ቢሆን አጋጣሚው ጥሩ ነው። የተሰወረባቸውን ኢትዮጵያዊነት ማለት ተረት ተረት አለመሆኑን ደማቸው የሚናገረው ኢትዮጵያውያን ባሳዩት የበቃን ሁለገብ መረቅ የሆነ ተግባር የተባ ተሳትፎ ከእንጉልቻቸው አባንኖቸዋል …

እኔነት፤ እኛነት የጠፉባቸው … እራሳቸውን በራሳቸው መርምረው ፈውሱን ፍለጋ እንዲንቀሳቀሱ ፈር ቀይሶላቸዋል። በሌላ በኩልም አብረው መራመድ ካልቻሉ  ዜግነታቸው ከበላያቸው እንደሚተን ተምረውበታል። በቃ ማለት በቃ ነው እና!

ሌላው የፀረ - ወያኔው ቤተሰቦች ሆነው፤ ግን አንዳንድ ጠንጋራ አስተሳሰብ የአላቸው ወገኖች የሌሎችን ህሊና በመጥለፍ በተለያዩ ዘዴዎች እያምታቱ በእምቅ ፍላጎት ፋታ በመንሳት ሌሎችን መሀል ላይ ገትረው ሚዛን ወደ ደፋው ላጥ ለሚሉት ወገኖች ድግሞ ድምኖባቸዋል።

የሰሞናቱ የግንቦት 7 ሕዝባዊ ስብሰባዎች ተስፋን ፋላጊ ሆነው ግን በተለያየ ምክንየት ተተብትበው ለነበሩትም ቢሆን ሚዛን አልቦሹን ወዝዋዛ ንጥ ስሜት በማሰወገድ ትግሉን እንዲቀላቀሉ አድርጓል።

ስለሆነም ተግባሩ ቀጥሎ በየአካባቢው ያሉ ወገኖች በተገኘው ኃይል እና ጉልበት መድረኮችን በማዘጋጀት ከዜግነት ጋራ እንዲፈታተሹ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን ቸል ሊሉት አይገባም።

በተጨማሪም ክንውኖችን እንደ ዳዊት እየደጋገሙ መሰለስ፣ መቀደስ በማወዳደስ ብቻ በራሱ ግብ ሊሆን ሰለማይችል ከህሊና መሰናዶው ተከታታይ ተግባራትን ጎን ለጎን ማጣደፍ ያስፈልጋል።

ጎልተው የወጡትን የፖለቲካ ድርጅቶች በሁሉም መስክ አጠናክሮ አጥቂ የማድረጉ ተግባር መቀጠል ይገባል። የፊት ለፊታችን ተግባር የገቢ ምንጭ ሊያሰገኙ የሚችሉ ዝግጅቶችን በሥርዓት በማደራጀት እና በመምራት በሙሉ ልብ፤ በሙሉ የሎጅስቲክስ ድጋፍ ከንቅናቄው ጎን መሰለፍ ያሰፈልጋል!

ማጠቃለያ … ዜግነቱ ጥቁር ለለበሰበት ወገን ህሊናውን አሰናድቶ በፍጥነት ተግባር ውስጥ መግባት የሚያስችለውን የህሊና ስንቅ ከፓርቲው ሕዝባዊ ስበሰባዎች ብቻ መጠበቅ ደግሞ የተገባ አይደለም።

የግል ጥረት መኖር አስፈላጊ ነው። ማንበብ አሁንም ማንበብ! ጭራ ሳይሆኑ ከወቅቱ እና ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር እራስን ማዋሀድ! የአንድ ሕዝባዊ ፓርቲ ሠራዊት መቅድመ ብጡለ ተግባር መሆን ይገባዋል። በስማ በለው አባል ነኝ ደጋፊ ነኝ ማለት ግን ግልብነት ይመስለኛል! ወደ ተግባር ለመሸጋገርም ዳጥ …

በቃን እዲበቃ ለተግባረ ተክሊል እናብቃው!